ይበላው ካጣ ፣ ይበላበት ያጣ ።

ይበጃል ያሉት መድሀኒት አይን አጠፋ ።

ይበጃል ያሉት ኩል አይን አጠፋ ።

ይብራና ይብራ ፣ ተጣሉ በሰው ሽንብራ ።

ይታደሷል እንጂ ይታገሷል ?

ይች ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም ።

## - ደ -

ደህና ሲታጣ ፣ ይመለመላል ጎባጣ ።

ደህና ወገን ያጣ ፣ ወየው ያለበት ጣጣ ።

ደህና ጦር ያለው ፣ ለግምብ ይሞክረው ።

ደመና ለዝናብ ፣ ድግስ ለሆዳም ።

ደመና በሰማይ ፣ የጨዋ ልጅ በአደባባይ ።

ደመና የጨበጠ ፣ ሰማይ የቧጠጠ የለም ።

ደም ቢያለቅሱ ፣ ድንጋይ ቢነክሱ ።

ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈሩም ።

ደም ተበክለህ ዝንብን አትጥላ ።

ደሞዙ ስንዴ ፣ ስራው የምን ግዴ ።

ደሞዝ ያጣ ሎሌ ፣ ይከበልላል በሃምሌ ።

ደሞዝተኛ ፣ አርፈህ አትተኛ ።

ደረስሁ ልጅ ፣ ፈላሁ ጠጅ ።

ደረቅ ይቀመጠላል ፣ እርጥብ ይጎብጣል ።

ደረቴን ቢያመኝ ፣ እግሬን አገመኝ ።

ደረጃ ለፍቶ መሄጃ ።

ደስታ ፣ በሽታ ።

ደስታና መከራ ፣ ቀኝና ግራ ።

ደባ ራሱን ፣ ስለት ድጉሱን ።

ደባል ሲሰነብት ፣ ይሆናል ባለቤት ።

ደባልና ሹመት ፣ ያለሰበብ አይሄድ ።

ደብር ለላስታ ፣ ድግድግታ ለጌታ ።

ደብተራ ሲኮራ ፣ እቤተ ክርስቲያን ገብቶ ጭራ ይይዛል ።

ደብተራ ፣ የዘኬ ኅተራ ።

ደብተራ የዘኬ ኅተራ ፣ ዘኬውን ሲቋጥር አነቀው ነብር ።

ደብተራና ተማሪ ፣ ሰናፊልና ሱሪ ።

ደንቆሮ ከሚያጫውተኝ ፣ የሚሰማ ያውጋኝ ።

ደንቆሮ የሰማ ለት ያብዳል ።

ደወል ላንበሳ ባማረለት ፣ ታድያ ማን ይሰርለት ።

ደጃቸውን አይዘጉ ሰውን ሌባ ይላሉ ።

ደጃፉን ጥሎ በጓሮ ይመጣል ።

ደገኛ ሲያርስ ፣ ቆለኛ ያነፍስ ።

ደጉ ነገር ሳያልቅ ፣ ከፉ መናገር ።

ደግ ጌታ ሲለግስ ፣ እንደ ፏፏቴ ያርስ ።

ደግ ኅረቤት ውሻና ድሙት ያሳድጋል ።

ደግና ማለፊያ ፣ ትግልና ልፊያ ።

ደፋር ሴት ጉልቻ ረግጣ ትወጣለች ።

ደፋር ወጥ ያውቃል ።

ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም ።

ዱላ ለባለጌ ፣ ምርኩዝ ለአሮጌ ።

ዱላን ይዞ ሌባን መጠየቅ ።

ዱባ ባገሩ ፣ ጋን ያህላል አሉ ።

ዱባና ቅል ፣ አበቃቀሉ አንድ ይመስላል ፤ አበላሉ ፣ ለየቅሉ ።

ዱባና ቅል አብሮ ይበቅል ፣ አበላሉ ፣ እየቅል ።

ዱባና ቅል ፣ አበቃቀሉ እየቅል ።

ዲያቆን ሲጠግብ በጧፍ ይማታል ፣ ወይፈን ሲቦርቅ ድንበር ያፈርሳል ።

ዲያቆን ከዘፈነ ፣ ፍየል ከቀዘነ ።

ዳር ሲፈታ ፣ መሀል ዳር ይሆናል ።

ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን ፣ ዳገት ሲወጡ ጥግ ጥጉን ።

ዳቦ በገና ፣ ቡና በጀበና ።

ዳቦ ካልበሉት ድንጋይ ፣ ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ ።

ዳቦ ያለ ቅርፊት ፣ ጠላ ያለ ምርጊት ።

ዳቦውን ጎርሶ ፣ ደሙን አብሶ ።

ዳተኛ በሬ ሀብታም ነው ።

ዳኛ ለዳኛ ያወርሳል ፣ ጉም ተራራ ያለብሳል ።

ዳኛ ምን ያደላ ፣ ከተረታ ሊበላ ።

ዳኛ ሲመረምር ፣ ከራስ ይዞ እስከ እግር ።

ዳኛ ሲቆጣ ማር ይዞ ከደጁ ።

ዳኛ ሲያዳላ በዳኛ ፥ አህያ ሲያጋድል በመጫኛ ።

ዳኛ ሲገኝ ተናገር ፥ ውሃ ሲጠራ ተሻገር ።

ዳኛ ስበር ፥ በእጅ ክበር ።

ዳኛ ቢንቁ ፥ የተያዘ እህልን ይወቁ ።

ዳኛ ቢያዳላ በዳኛ ፥ አህያ ቢያጋድል በመጨኛ ።

ዳኛ ቢያጋድል በዳኛ ፥ አህያ ቢያጋድል በመጫኛ ።

ዳኛ አውጥቼ ፥ ዘንግ አቅንቼ ።

ዳኛ አይነቀፍ ፥ እሳት አይታቀፍ ።

ዳኛ ካዳላ ጭነት ቀላል ።

ዳኛ የወል ፥ ምሰሶ የመካከል ።

ዳኛ የፈረደበት ፥ መርከብ የተሰበረበት ።

ዳኛ የፈረደው ፥ ስለት የቀደደው ።

ዳኛ ያዳላበት ፥ እሳት የበላበት ።

ዳኛ ያፈሰሱለት ፥ ፈረስ ያከሰከሱለት ።

ዳኛ ይመረምራል ፥ ጣዝማ ይሰረስራል ።

ዳኛ ፍርድ አይከላ ፥ እህል ጎታ ይሞላ ።

ዳኞች ከመረመሩ ፥ ይናገራል ምድሩ ፥ ይገኛል ነገሩ ።

ዳኞች ከመረመሩ ፥ ይገኛል ነገሩ ።

ዳዊትን ያህል መዝሙር ፥ ጨለማን ያህል ጥቁር የለም ።

ዳገት ሲወጡ ጥግ ጥጉን ፥ ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን ።

ዳገት እርሙ ፥ ሜዳ ወንድሙ ።

ድሃ ለወዳጁ አይሰንፍ ፥ ሀብታም ካለወዳጁ አይተርፍ ።

ድሃ ሲቀልጥ ፣ አመድ አመድ ይሸታል ።

ድሃ ሲቀመጥ እጁን ይዘህ አወዛውዘው ።

ድሀ ሲቀማጠል ፣ ከወገቡ ቀምጠል ።

ድሃ ሲቆጣ እግሩ ይፈናጠራል ።

ድሃ ሲቆጣ ከንፈሩ ያብጣል ፣ መንገዱን ያሰልጣል ።

ድሃ ሲንቀባረር ፣ ያለቀሰ ይመስላል ።

ድሃ ቅቤ ወዶ ፣ ማን ሊሸከም ነዶ ።

ድሃ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ፣ እከክ ይጨርሰው ነበር ።

ድሃ በጉልበቱ ፣ ባለፀጋ በሀብቱ ።

ድሃ ባይ አይኔን አመመኝ ።

ድሃ ተበድሎ ፣ ማሩኝ ይላል ቶሎ ።

ድሃ ተበድሎ ራሱ ይታረቃል ፣ ሀብታም በድሎ ተመልሶ ይስቃል ።

ድሃ ከንቡ ይዳላ ።

ድሃ ካለቀሰ ፣ ቀኑ መች አነሰ ።

ድሃ ካልሰራ ፣ ዶሮ ካልጫረ ።

ድሃ ካልዘራ ዶሮ ካልጫረ ፣ ማን ያበላው ነበረ ።

ድሃ ውሃውን ጠጥቶ እሳቱን ይሞቃል ፣ ሃብታም ስለ ገንዘቡ ይጨነቃል ።

ድሃ የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም ።

ድሃ በጉልበቱ ፣ ባለፀጋ በከብቱ ።

ድሃ ያልፍልኛል ይላል ፣ ጌታ ቀኑን ይቆጥራል ።

ድሃ ያመልከት ፣ ዳኛ ያሟግት ።

ድሃ ያመልከት ፣ ዳኛ ያሟግት ።

ድሃና ሹም ተማግቶ ፡ ድንጋይና ቅል ተማትቶ ፤ የማይሆን ነው ከቶ ።

ድሃና እመቤት ፡ እልፍኝና ማድቤት ።

ድሃና ጌታ ተሟግቶ ፡ ድንጋይና ቅል ተማትቶ ።

ድሃና ጌታ ተሟግቶ ፡ ድንጋይና ቅል ተማትቶ ፡ የማይሆን ነው ከቶ ።

ድሃን ምን ትሰራለህ እንጂ ፡ ምን ትበላለህ የሚለው የለም ።

ድሃን ሲያስለቅሱ ፡ ከሰላሴ ይወቀሱ ፡ መንግስተ ሰማያትን አይወርሱ ።

ድሃን ካስለቀሱ ፡ በስላሴ ዘንድ ይወቀሱ ።

ድህነት ፡ ከአምላክ መሰማማት ።

ድል በመታደል ፡ ሙያ በመጋደል ።

ድል አድል ፡ በአንድ ድልድል ።

ድመት መንኩሳ ፡ አመሏን አትረሳ ።

ድመት በታች ከሆነች ፡ ውሻ ታሸንፋለች ።

ድመትና አይጥ ፡ እሳትና ጭድ ።

ድመትን በቆሎ መጠርጠር ።

ድመትን አይጥ ገደለቻት ፡ ወይ ጥቃት ወይ ጥቃት ።

ድምቢጥ እንደ አቋሟ በብር ትታገማለች ።

ድምፅና ቁንጫ ባዶ ቤት ይወዳል ።

ድራቶ ከነቅማሉ ፡ መጥፎ ሰው ከነአመሉ ፡ ወዲያ በሉ ።

ድሪያ የዝሙት ዋዜማ ።

ድር ቢያብር ፡ አንበሳ ያስር ።

ድርብርብ ፡ እንደ ደጋ ንብ ።

ድርና ማግ ፡ ለሀጭና ልጋግ ።

ድርጎ ራቱ ፣ ድርጎ ቢቀር ሞቱ ።

ድርጎ የለመደች መበለት ፣ ወተት ያየች ድመት ።

ድርጭት ፈንጠር ፣ ምዝግዝግ ጎንደር ።

ድሮ ካያታችን ፣ ካጤ ነው ትውልዳችን ።

ድበላ ፣ አንዳንድ ጊዜ ይበላ ።

ድንቁርና ከልብህ መካከል ተራራ ያህል ።

ድንኳን ያየ ባለጌ ።

ድንኳን ገልጦ ፣ ዙፋን ረግጦ ።

ድንኳን ገልጦ ፣ ዙፋን አጊጦ ።

ድንጉተኛ ስህተት ፣ የቁልቁለት ውድቀት ።

ድንጋይ ላይ ተቀማጭ ፣ የባለጌ ተለጣጭ ።

ድንጋይ በድንጋይ ላይ ትልቅ ቤት ይሆናል ።

ድንጋይ ወርዶ እዘብጥ ያርፋል ፣ ያገኘው ይተርፋል ።

ድንጋይን ለረገጠ ፍለጋ የለው ፣ ውሃን ለጠጣ ሽታ የለው ።

ድግርና ገባር ፣ ሲተካከል ያምር ።

ድግስ የሌለው ዋዜማ ፣ ምልክት የሌለው ዜማ ።

ድጥ ማንሸራተቱን ፣ ባለጌ ማሽሟጠጡን አይተውም ።

ዶማ ለመማሻ ፣ ማረሻ ለመፈለሻ ።

ዶሮ ላትበላው ታፈስ ።

ዶሮ ፣ ልጇቿን ይዛ ጓሮ ለጓሮ ።

ዶሮ ሲሉ ሰምታ ፣ ሞተች ከጢስ ገብታ ።

ዶሮ በልቶ ከብስና ፣ ጎመን በልቶ በጤና ።

ዶሮ በልጅዋ እንጀት ትጫወታለች ።

ዶሮ በማሰር ፥ ገደል ለዝንጀሮ ።

ዶሮ በጋን ።

ዶሮ ቢጠፉ ከቤቱ ፥ መነኮሰች እናቱ ።

ዶሮ ብትታመም በግ አረዱላት ።

ዶሮ አንዱን እንቁላል በወለደችበት ወታቦ ትሞላለች ።

ዶሮ እኔ ባልበላ ጭሬ አላፈስም ወይ አለች ።

ዶሮ ከቆጥ ፥ በሬ ከጋጥ ።

ዶሮ ከቤት ውላ ዝናብ ይመታታል ።

ዶሮ ከጋጥ ፥ በሬ ከቆጥ ።

ዶሮ ከጮኸ ሌሊት ፥ ከደብረታቦር ወዲያ ክረምት የለም ።

ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት ፥ ከቡሄ ወዲያ የለም ክረምት ።

ዶሮ ካልበሏት ፥ አሞራ ናት ።

ዶሮ ጭራ ማረጃዋን አወጣች ።

ዶሮ ጭራ የምታወጣው ምስጢር ።

ዶሮ ጭራ ጭራ ፥ አወጣች ማረጃዋን ካራ ።

ዶሮና ቀበሮ ፥ ተገናኝቶ ጓሮ ።

ዶሮን ሲቀጣጠብዋት ፥ በመጫኛ ጣሏት ።

ዶሮን ሲደልሏት ፥ በመጫኛ ጣሏት ።

ዶሮን ቢያማት ፥ በሬ ተሳሉላት ።

# - ጀ -

ጀማሪ ይጥፋ ፣ ሰካራም ይትፋ ።

ጀምሮ የማይፈፅም ፣ ፈጭቶ የማያልም ።

ጀምሮ ይጨርሳል ፣ ለጉሞ ይተኩሳል ።

ጀምበር ሳለ ሩጥ ፣ አባት ሳለ አጊጥ ።

ጀርባ ለባለቤቱ ባእድ ነው ።

ጀርባዬን አሳክከኝ ፣ ተንጠራርቼ ማከክ ተሳነኝ ።

ጀርባዬን እከከኝ ለኔ ራቀኝ ።

ጀግና የሚታወሰው ወይም ከሞተ ወይም ከተለየ በሁዋላ ነው ።

ጃርት ያስደነገጠው ዱባ ይመስላል ።

ጅምር ይጨረሳል ፣ ልጉም ይተኮሳል ።

ጅምርን ለነገ አያሳዩም ።

ጅራትና ሀሜት በስተሁዋላ ነው ።

ጅራቷ ፣ ታደርሳለች ከናቷ ።

ጅራፍ መትቶ ያለቅሳል ፣ ባለፀጋ በድሎ ተመልሶ ይወቅሳል ።

ጅራፍ እሱው ይገርፍ ፣ እሱው ይለፍ ።

ጅብ ምን ይመስላል ? እግሩ ያነክሳል ፣ አፉ ይነክሳል ።

ጅብ ሲበላህ በልተኸው ተቀደስ ።

ጅብ ባጥንት የተገደገደ ፣ በጅማት የተማገረ ቤት አለ ቢሉት ፣ ወዴት ነው ሳይል ገደል ገብቶ ሞተ ።

ጅብ አያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል ።

ጅብ እስኪነክስ ፣ ያነክስ ።

ጅብ እንኳን ጓደኛውን ይጣራል ።

ጅብ እንደ ቁመቱ ልብ የለውም ።

ጅብ እንደ አባቱ ይዘርጥጥ ።

ጅብ እንደ አባቱ ይዘርጥጥ ፤ አህያ እንደአባቱ ይፈርጥጥ ።

ጅብ እንደ አገሩ ይጮሃል ።

ጅብ እንደ ጉልበቱ ልብ የለውም ።

ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ።

ጅብ ከላይ ውሃ ሲጠጣ ፤ ታች ያለችውን አህያ አታደፍርሽብኝ አለ ።

ጅብ የኔ ነው ስለው ወናፌን ቀማኝ ።

ጅብና ሸማኔ ከጉድጓድ አይወጡም ።

ጅብና እህል ሳይተዋወቁ ይኖራሉ ።

ጅብን ሊወጉ ፤ ባህያ ይጠጉ ።

ጅብን ፈርቼ ከዛፍ ብወጣ ነብር ቆየኝ ።

ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው ።

ጆሮ በላ ፤ ሆድ ጠሙን አደረ ።

ጆሮ ባይጠም ፤ ይመስላል ሆዳም ።

ጆሮ አይጠምም ፤ አይን አይጠግብም ።

ጆሮ እዳውን አይሰማም ።

ጆሮ ካያት ያረጃል ።

ጆሮ የሰማውን ፤ ለማየት ይሄዳል አይን ።

ጆሮ የሰማውን ፤ ልብ ያውቀዋል ።

ጆሮ የቀድሞዎቹ እኩያ ነው ።

ጆሮውን ቢቆርጡት ፤ መስሚያው ይቀራል ።

- ገ -

ገላጋይ አጥቼ ግልገሌን በላሁዋት ።

ገለፈንት ፣ የቤት ጋለሞታ ።

ገመድን ሲበጠስ መቀጠል ፣ አባይ መስካሪን ገደል ።

ገራገሩን ተጫውቶ ፣ ይኖሯል ተስማምቶ ።

ገር ገሩን ተጫውቶ ፣ ይበሏል ተስማምቶ ።

ገርነት ፣ የእግዜር ቸርነት ።

ገርነት ፣ ያገባል ገነት ።

ገርና ልል ፣ ሙዳይና አገልግል ።

ገርን ልጅ እናቱ አትወደውም ።

ገበሬ አቆጣጠረኝ ፣ ወታደር አወራወረኝ ።

ገበሬ አከባሪውን ፣ ባለጌ መካሪውን ይጠላል ።

ገበሬ አከባሪውን ይጠላል ።

ገበያ ቢመቻት ፣ ልጅዋን ሸጠቻት ።

ገበያ ነሽ ብለው ይሻሻጡብሻል ።

ገበያ እንደሰጠህ እንጂ ፣ እናትህ እንደላከችህ አይሆንም ።

ገበያ እንዴት ዋለ? ቢለው ፣ አንዱ ባንዱ ሲስቅ ።

ገበያ የሚሰጥን እናት አትሰጥም ።

ገበጣ ላዋቂ ፣ ወሬ ለጠያቂ ።

ገበጣ ላዋቂ ፣ ወሬ ለጠያቂ ፣ ዋዛ ፈዛዛ ለሳቂ ።

ገቢ ያፈርሳል ፣ ቀዳዳ ያፈሳል ።

ገቢውን ባለቤት ያውቃል ።

ገባ ወጣ ፤ ነገር ያመጣ ።

ገባር ያህያ ግምባር ።

ገብሬል ያየው ምስጢር ።

ገብስ ሲበስል ፤ አባቱን ይመስል ።

ገብስና ሽንኩርት ቂጡ ሲበስል ነው ።

ገብስና ገብስ አብሮ ይነፈስ ።

ገና ዘንቦ ባርቶ ።

ገናም በሙከቱ ፤ ሁዳዴም በእልበቱ ይታወቃል ።

ገናና ጥምቀት ፤ እኩል አውዳመት ።

ገንዘቡ የሰው ቢሆን ፤ አዳዩ የኔ ይሁን ።

ገንዘቤ አትውጪ ከቤቴ ፤ ታጣይኛለሽ ከጎረቤቴ ።

ገንዘብ ከጄ ፤ ዘመድ ከደጄ ።

ገንዘብ ከጅ ከወጣ ፤ ያመጣል ጣጣ ።

ገንዘብ ከጅ ከወጣ ፤ ይመጣል ይዞ ጣጣ ።

ገንዘብ ከጅ ፤ ዘመድ ከደጅ ።

ገንዘብ ካለ ፤ በሰማይ መንገድ አለ ።

ገንዘብ የልብ ስር ነው ።

ገንዘብ የጠፋበት ፤ ብዙ ሀጢአት አለበት ።

ገንዘብ ያልያዘ መንገደኛ ፤ አይፈራም ቀማኛ ።

ገንፎ ለጉንፋን ይበጃል ፤ ወዲህም ለሆድ ይበጃል ።

ገንፎ ለጉንፋን ደግ ነው ፤ እግረ መንገዱንም ለሆድ ይበጃል ።

ገንፎ ማላመጥ ፤ በእግዜር ማልመጥ ።

ገንፎ ስርታ ለራት ፣ ቢያጎርሳት ተኮሳት ።

ገንፎ ሲበሉ ልጅ አስወግዶ ፣ ጠላ ሲጠጡ እሳት አንድዶ ።

ገንፎ በድስት ፣ ጎመን በምንቸት ።

ገንፎ እፍ እፍ ቢሉሽ ፣ ሊውጡሽ ነው እውነት አይምሰልሽ ።

ገዝቶ የማይቆጣ ፣ አጥቦ የማያነጣ ።

ገደል ለዝንጀሮ ፣ ጉድጓድ ለቀበሮ ።

ገዳም የገባ አይወጣ ፣ ከል የገባ አይነጣ ።

ገዳይ ቢያረፍድ ፣ ሟች ይገሰግሳል ።

ገዴ ገድሽ ለኔ ፣ ስጋሽ ለአረመኔ ።

ገድለው ካላመለጡ ፣ ምንድነው ጌጡ ።

ገድሎ ነበር ሞተ ።

ገድሎ ባለቃዬ ፣ ከሶ ከጠበቃዬ ።

ገጣባ አህያ ትሰለቻለች ፣ ጭና ታበላለች ።

ገጣጣ ሲሞት የሳቀ ይመስላል ።

ጉልበት አለኝ የበላ ፣ ምላስ አለኝ ፣ የሰላ ።

ጉልበት አለኝ የዝሆን ፣ አፍ አለኝ ላንተ የሚሆን ።

ጉልበት አለኝ የዝሆን ፣ አፍ አለኝ የመስፍን ።

ጉልበት አለኝ የዝሆን ፣ አፍ አለኝ የመኮንን ።

ጉልበት የሌለው ወንበዴ ፣ ትርፍ የሌለው ነጋዴ ።

ጉልበት የሌላት ወይዘሮ ፣ ገደል የሌለው ዝንጀሮ ።

ጉልቻ የላቀው ፣ አመድ ያጠለቀው ።

ጉልቻ የላቀኝ ፣ አመድ ያጠለቀኝ ፣ አለ አማኑኤል ማን ጠየቀኝ ።

ጉም ሲለቅ ፤ የታባትህ ትገባ አንተ ሌባ ፡፡

ጉም መጣመጥ ፤ ውሃ መጣመጥ ፡፡

ጉም ተራራን ያለብሳል ፤ ሹም ለሹም ያወርሳል ፡፡

ጉሬዛ ቢውል ከጠጣ ፤ ጥፋት ለምዶ መጣ ፡፡

ጉሮሮ የሚወጠውን ፤ እጅ ይመጥነዋል ፡፡

ጉቦ የለመደ ዳኛ ፤ አህያ የለመደ ጅብ አንድ ነው ፡፡

ጉቦና ሌባ በር አይወድም ፡፡

ጉትቻ ለጆሮ ትንሽ ትመስላለች ፤ ዛፍ ጎበዝ ትቆጥራለች ፡፡

ጉትቻ ለጆሮ ፤ እልፍኝ ለወይዘሮ ፡፡

ጉትቻ ለጆሮ ፤ ጥሬ ለዶሮ ፡፡

ጉንዳን ባልንጀራው ሲሞት ፤ ብቻውን ተሸክሞ ይዞራል ፡፡

ጉንዳን ፤ ቤቱን ይመራል ፡፡

ጉንዳን የባልንጀራውን ሬሳ ፤ ብቻውን ያነሳ ፡፡

ጉንፋን የተያዘና ፍየል ይዞ የተደበቀ ፤ ሳይጋለጥ አይቀርም ፡፡

ጉደኛ ውሻ ፤ ስጋ ተቀምጠ ቆሎ ትሻ ፡፡

ጉዳት ከመጣ ፤ መካር አይታጣ ፡፡

ጉዳይ ሳይኖርህ ገበያ አትውረድ ፤ ያንዱን ነገር ሰምተህ አትፍረድ ፡፡

ጉዳይ አሳልፍ እንድትታማ ፤ አሮጌ ሁን ልትፎክር ፤ ሙት ልትመሰገን ፡፡

ጉዳይ የሌለህ ገበያ አትውረድ ፤ ያንዱን ሰው ነገር ሰምተህ አትፍረድ ፡፡

ጉድ ለባለቤቱ ልግም በገላ ነው ፡፡

ጉድ ለባለቤቱ ያንገት ልብስ ነው ፡፡

ጉድ እንግዳ ነገር ፤ አሳድሮ መቸገር ፡፡

ጉድ ያለው ገንፎ አድሮ ይፋጃል ።

ጉድ ይገርማል ፣ አሀያ ከጅብ ይከርማል ።

ጉድ ይገርማል ፣ ጅብ ከአሀያ ጋር እንዴት ይከርማል ።

ጉድሽ ድንቅሽ ፣ ና ብለሽ ወዴት ሄድሽ ።

ጉድነሽ ያንኮበር ቅጠል እያደር ትለበለቢያለሽ ።

ጉድና ብርቅ ፣ እስከ ሶስት ቀን ያስጨንቅ ።

ጉድና ድንቅ ፣ አለ አንድ ጊዜም አይደምቅ ።

ጉድና ድንቅ አንድ ሰሞን ነው ።

ጉድና ጅራት በስተሁዋላ ነው ።

ጉድጓድ በራሱ አፈር አይሞላም ።

ጉጉት ብትጠቃ ፣ እርኩም ሆነ ጠበቃ ።

ጉፋያ ሲነዱ ፣ ይሸከሙ ።

ጉፋያ ከመብላት ፣ ስብ መሸከም ይሻላል ።

ጉፋያ ከመብላት ፣ ሙጣ መሸከም ።

ጉፋያ ከሚያርዱ ፣ ስብ ይቀላውጡ ።

ጉፋያን ሲበሉ ፣ ስብ ይቀላውጡ ።

ጊዜ ሲከዳ ፣ መሬቱ ያድጣል ።

ጊዜ ወርቅ ነው ፤ ግን ሃላፊ ነው ።

ጊዜ የሌለው የለም ፤ ግን ከእድሉ የሚያልፍ የለም ።

ጊዜ የሰጠው ቅል ፣ ድንጋይ ይሰብራል ።

ጊዜ የሰጣት አይጥ ከፈረሰኛ እኩል ትሮጣለች ።

ጊዜ ያለው ፣ ጊዜ አይጠብቅ ።

ጋለሞታና ጌታ ፥ ደጅ የጠኑለታ ።

ጋሬና ጉባ ፥ ቅልና ዱባ ።

ጋሻ ለማንባር ፥ ጫማ ለጠጠር ።

ጋሻ እሰጥ ጋሻ እሰጥ ሲሉ ጦር አገባ ።

ጋሻ ፥ ዱሮ ቀረሻ ።

ጋሻና ውጊያ እንዴት ነው፣ ቢለው ፥ ጋሻ ወርውሮ ጦር መመከት ነው አለ ።

ጋሻና ማንባር አይሸሸግም ።

ጋን ሰሪ ፥ ምጣድ አይዋጣለትም ።

ጋን ሲለቀለቅ ፥ ማድጋን ይሞላል ።

ጋን ሲያሚዋጡት ፥ ምንቸት ይሞላል ።

ጋን ቢያንጫልጡት ፥ ማሰሮ ይሞላል ።

ጋኖች አለቁና ፥ ምንቸቶች ጋን ሆኑ ።

ጋይ የለ እሸት ፥ ስጡኝ አለ ።

ጋጋሪ ያበስላል ፥ ተናጋሪ ያስመስላል ።

ጌታ ሁን ፥ እንዳሻህ ሁን ።

ጌታ ሁን ፥ እንደፈቀደህ ሁን ።

ጌታ ለሎሌው ፥ ነጋዴ ላሞሌው ያስባል ።

ጌታ ሲሰጥ ፥ ማን ይከለክላል ።

ጌታ ሲወድ ማን ይጠላል ፥ ጌታ ሲሰጥ ማን ይከለክላል ።

ጌታ ቢጫወት ፥ ያልኮራ ይመስላል ።

ጌታ ባወቀው ይፈርዳል ፤ ሰው ባላወቀው ይጎዳል ።

ጌታ የለቁን ፥ አባት የመሰረቱን ።

ጌታ ያዛል ፣ ውሃ ይለዛል ።

ጌታ ያዛል ፣ ውሃ ያንዘዛል ።

ጌታና ሎሌ ተጣልተው ፣ ዱባና ቅል ተማተው ፣ ኧረ አይመስልም ተው!!

ጌታና ሎሌ ተጣልቶ ፣ ቅልና ድንጋይ ተማቶ ።

ጌታና ገቢታ አቅራቢ ነው ፣ ሰጭው እግዜር ነው ።

ጌታና ጋለሞታ ፣ ደጅ የጠኑ ለታ ።

ጌታዋን የምታምን ውሻ ፣ ፍሪዳ ሲታረድ እወንዝ ወረደች ።

ጌታዋን የምትወድ ላም በመስከረም ትወልዳለች ።

ጌታዬ ምን አልኩህ ? ጠጅ አጠጥተህ ውሃ ።

ጌታዬ ካሉበት እገሙኝ ።

ግልግልና ገንፎ ትኩሱን አያስገባም ።

ግመል ምን ተጭነሃል? ሽመል ፤ ምን ያወዛውዝሃል? አመል ።

ግመል ሰርቆ አጎንብሶ ሄደ ።

ግማሹን ተላጭታ ፣ ግማሹን ተቀብታ ።

ግማሽ ልጩ ፣ ግማሽ ጎፈሬ ።

ግም ለግም ፣ አብረህ አዝግም ።

ግረፍ ፣ ከባት አትለፍ ።

ግራ መብል ፣ ቀን ገንፎ ፣ ሌሊት ድፎ ።

ግራ መብል ፣ ቀን ገንፎ ሌሊት ዶሮ ።

ግራ ነገር ፣ ከወንዝ ማዶ ፍቅር ፣ ከጎረቤት ጥል ።

ግርግርታ ፣ የሌባ ደስታ ።

ግባ ያላለው ገንዘብ ፣ አጥር ቀዶ ይወጣል ።

ግብ እንደግቡ ፤ ሙክት እንደ ስቡ ።

ግብር እስከ መቃብር ።

ግብር ይውጣ ።

ግብር ይውጣ ፤ የማይቀር እዳ ።

ግብዝና ፤ መቼ እንደ ጺቁና ።

ግብዝን ሁለት ጊዜ እባብ ነከሰው ።

ግንብና ድንጋይ ፤ ጌታና አባይ ።

ግንቦት ቢዳምን የሚዘንብ ይመስላል ፤ አሮጌ ቢፎክር የሚዋጋ ይመስላል ።

ግንቦት ቢዳምን ይዘንብ ይመስላል ፤ ሃምሌ ቢባራ በጋ ይመስላል ።

ግንድ ለሺ አይከብድም ።

ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰበኝ ።

ግዳይ ለከንፈሬ ፤ ጥምጥም ለምምሬ ።

ግዳይ አምሯቸው ዘመቱ ፤ እሳቸውም ሞቱ ።

ግፈኛ ፤ የሰይጣን መላከተኛ ።

ግፍ ሲቆም ፤ ፀሎት አያሻም ።

ግፍ ሲናኝ ኩበት ፤ ሲጠልቅ ድንጋይ ይዋኝ ።

ግፍ ባገር ሲሞላ ፤ ርስ በርስ ያባላ ።

ግፍ ባገር ሲናኝ ኩበት ፤ ጠልቆ ድንጋይ ይዋኝ ።

ግፍ አይፈሬ መሬት ፤ እንክርዳድ ያበቅላል ።

ግፍ የተሰራ በኛ ፤ ካሱ ይሉናል በዳኛ ።

ግፍስ በባህር ይመላል ፤ እሳ አሳውን ይበላል ።

ኀልማሳ ሲታጠቅ ከደረቱ ፣ ሲሮጥ ከጉልበቱ ።

ኀልማሳ እበቀለበት ላም አይማረክም ፤ ሽማግሌ እበቀለበት ነገር አይሳሳትም ።

ኀልማሳ ካለበት ከብት አይሰረቅ ፣ ሽማግሌ ካለበት ነገር አይነጠቅ ።

ኀልማሳ ካለበት ከብት አይነጠቅ ፣ ሽማግሌ ከዋለበት ነገር አይወድቅ ።

ኀመን በጤና ።

ኀመን ባወጣው ነፍስ ፣ አትኩራ ገብስ ።

ኀረምሳ ፣ እንደበላህ አንሳ ።

ኀረቤት አያውቀው ነገር ፣ ወንጠፍት አያጠራው አሰር ።

ኀረቤት ፣ ይሆናል ጠላት ።

ኀረቤት ይሆናል ጠላት ፣ ያችን ሴት አትዝጊ በሷት ።

ኀራዴ ለወንበዴ ፣ ሱቅ ለነጋዴ ።

ኀራዴህ ኀመዳም ፣ ሚስትህ አመዳም ።

ኀራዴና ምስጥ ፣ ውስጥ ለውስጥ ።

ኀርፍ ሲወስድ እያሳሳቀ ፣ ተንኮለኛ ሰው ሲጎዳ እየተራቀቀ ነው ።

ኀሽ ለልጅዋ ብላ ትወጋ ።

ኀሽ ጠመድኩ ይሆናል ብዬ ፣ ፈትቼ ሰደድኩ አይሆንም ብዬ ።

ኀበዝ ፊት ሰማይ ሰማይ ያያል ፣ ሁዋላ ምድር ምድር ያያል ።

ኀባጣን ሲቀብሩ እንደ አመሉ ።

ኀባጣን ቀንና ቅምዝምዝምን አጎንብሰህ አሳልፈው ።

ኀባጣን ይቀብሩ ፣ እንደምግባሩ ።

ኀኑ የኔ ፣ ቀኑ ሰኔ ።

ኀንደር ወጣ ፣ ምን ይዞ መጣ ።

ጎንደር ወጣህ ፤ ምን አመጣህ ?

ጎንደር ወጣሽ ፤ ምን አመጣሽ ?

ጎዳ ከብት ከቀንዳም ይብሳል ።

ጎዳናና መንገድ ፤ ጉንጉንና ገመድ ።

ጎዳው ፍየል ፤ ቀንዳሙን ወጋው ።

ጎድሎ ነበር ሞላ ፤ ሞልቶ ነበር ፈላ ።

ጎጃም በዘነበ ፤ ሳይንት እህል ሆነ ።

ጎጆ ወጭ ሙሽራ ፤ በገፍ ወጥ ትሰራ ።

ጓሳና ድንግል ፤ ያላንድ ጊዜ አይበቅል ።

## - ጠ -

ጠላ በማቶቱ ፤ እንጀራ በሌማቱ ።

ጠላ ባለቤቱን አያውቅም ።

ጠላ ካስር ፤ ነገር ካገር ።

ጠላ ካሰከረው ፤ ወተት ያሰከረው ።

ጠላ ያለ አተላ ፤ ጠጅ ያለ አንቡላ ።

ጠላት በጥርስ ሲገኝ ።

ጠላት ቢያባብሉት ፤ ወዳጅ አይሆንም ።

ጠላት የሌለው ወዳጅ አያሻውም ።

ጠላት ፤ ይቀባል ጥላት ።

ጠላትህን ውሃ ሲወስደው ፤ እንትፍ ብለህ ጨምርበት ።

ጠላትን ለማግኘት ሲጎረጉሩ ፤ በወዳጅ ይጀምሩ ።

ጠላትን በጦር ፣ አባትን መጦር ።

ጠላና ጉተና እለቱን አይደርስም ።

ጠላኝ ማለት ያስጠላል ፣ ልግደል ማለት ያስገድላል ።

ጠላው ሳይገባ ማቶቱ ፣ ቀንዱ ሳይገባ ጅራቱ ።

ጠላው የባእድ ፣ አሳላፊው ዘመድ ።

ጠልቶ ለጠላት ፣ አስሮ ለእስራት ።

ጠመንጃ ያለ ጥይት ዱላ ፤ ወንድ ያለ ሴት ቀውላላ ።

ጠመንጃ ያለ ጥይት ዱላ ፤ ወንድ ያለ ሴት ድሃ ።

ጠመደና በሬና ዝሆን ፣ መቸም እንዳይሆን ።

ጠርቦ ለደጁ ፣ ፈርዶ ለልጁ ።

ጠርጥር ፣ ከምግቡ ውስጥ አለ ስንጥር ።

ጠቃሚ ከናሪያ ይመጣል ፣ አጥፊ ከጉልበት ይወጣል ።

ጠቋሚ ፣ ጠቃሚ ።

ጠበቃ ታፈጀ ፣ በርበሬ ታረጀ ።

ጠበቃና ቅል ባጠገብ ይውላል ።

ጠባ ለኪዳን ፣ መሸ ለቁርባን ።

ጠባቂ ያላት በግ ፣ ላቷ እደጅ ያድራል ።

ጠባብ አልጋ የግድ ያስተቃቅፋል ።

ጠብ ባለበት ቤት ፣ ዶሮ ትሞት ።

ጠብ ተጀመረ ፤ አንበሳ ላምን ሰበረ ።

ጠብ ተጀመረ ፤ ያ ልጅሽ አለ ልጁ ሲል የነበረ ።

ጠብ ካለበት ቤት ፣ ዶሮ ከጋጥ ትሞት ።

ጠብ የሻ መኮንን ፣ የዶሮ ሻጡኛ አም ይላል ።

ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም ።

ጠንቋይ ባያሳምን ፣ ያጠራጥር ።

ጠንቋይ አባይ ቤት ያስፈታል ።

ጠያቂ የለም እንጂ ከድሃ ምክር ይገኛል ።

ጠይብ በገል ይበላል ።

ጠጅ ለወረት ፣ ወዳጅ ለችግር ለት ።

ጠጅ ለጨዋ ልጅ መጫወቻው ፣ ለባለጌ ልጅ መማቻው ።

ጠጅ በብርሌ ፣ ነገር በምሳሌ ።

ጠጅ የሌለበት  አበጋዝነት ።

ጠጅ ፣ የወረት ወዳጅ ።

ጠጅ ይሻላል በመጠኑ ፣ የጨዋ ልጅ ይበልጣል በቀጭኑ ።

ጠጅና መኮንን ፣ ድሃና ጎመን ።

ጠገብሁ ያለውን ብላ አትብለው ፣ ፈራሁ ያለውን ድፈር አትበለው ።

ጠጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል ።

ጠፍር በሊታ ብትሄድ ፣ ልጓም በሊታ መጣች ።

ጠፍር መጫኛ ፣ ቁርበት መገኛ ።

ጡት መጥባት ፣ የናት ።

ጢም የሌለው መምህር ፣ አፀድ የሌለው ደብር ።

ጢም የሌለው መምህር ፣ አፀድ የሌለው ደብር ፣ አምሮም አያምር ።

ጢምህን እጠላለሁ ፣ መሳምህን እወዳለሁ ።

ጢሰኛ ሲቆይ ባለርስት ይሆናል ።

ጣል በደጅ ፣ እስር በፍንጅ ።

ጣመኝ ፣ ድገመኝ ።

ጣት ገማ ብሎ ፣ ቆርጦ አይጣልም ።

ጣዝማ ሰርሳሪ ፣ ዳኛ መርማሪ ።

ጣይ ያየውን ፣ ሰው ሳያየው አይቀርም ።

ጣጣ ፣ ፈንጣጣ ።

ጣጣ ፈንጣጣ ፣ ድንጋይ ፈለጣ ።

ጤና ከሀብት ፣ ወፍጮ ከከብት አይቆጠርም ።

ጤፍ መፍሰስሽን ቢያይ ፣ ገበሬ ባልዘራሽ ።

ጤፍ ቢሰኩ ፣ ሰማይን ቢያኩ ፣ አይገኝም ልኩ ።

ጤፍ አይቆላ ፣ የጭቃ ልጅ አይጠላ ።

ጤፍ አጎደለ ቢለው ፣ ገብስ እንዳይሰማ አለው ።

ጤፍ ከዘመዷ ፣ ጎታ ትሞላለች ።

ጤፍ ካላረሙ አይለማ ፤ ስጋ ካልሰነበተ አይገማ ።

ጥለውት የመጡትን ጓደኛ ዞረው አያዩትም ።

ጥላና ሸኝ ቤት አይገቡም ።

ጥል ያለሽ በዳቦ ።

ጥል ያጠላላ ፣ ኩስ ላፍ ይጠላ ።

ጥልቅ ብዬን ውሃ ወሰዳት ።

ጥምብ ባለበት ቁራ ይዞራል ።

ጥምድ እንደበሬ ፣ ቅንት እንደገበሬ ።

ጥምጥም የሌለው መምህር ፣ አፀድ የሌለው ደብር ።

ጥሩ መስሎ አተላ ፣ ፍሬ መስሎ ገለባ ።

ጥሩ እንደ ብርሌ ፣ ቀይ እንደ በርበሬ ።

ጥሩ ድህነት ጥሩ ነፃነት ፣ ጥሩ ሀብት መልካም ርስት ።

ጥሩ ጠላት ጥኑ ወዳጅ ይሆናል ።

ጥሬ ለዶሮ ፣ ግልግል ለቀበሮ ።

ጥሬና ክፉ ንግግር ፣ ሆድ ያሻክራል ።

ጥርስና ከናፍር ፣ ቢደጋገፍ ያምር ።

ጥርስና ከንፈር አብሮ ይደማል ።

ጥቂት ሀመም ታመህ ፣ ወዳጅ ጠላትህን እየው ።

ጥቂት ስጋ ፣ እንደ መርፌ ትወጋ ።

ጥቂት ሽሮ ፣ ማታ ዶሮ ።

ጥቂት ያላት ፣ እረፍት የላት ።

ጥቂት ያላት ፣ እንቅልፍ የላት ።

ጥቂት ጥቂት ኤሊም ትሄዳለች ፤ ካሰበችበት ትደርሳለች ።

ጥቃት ከጥንብ ይገማል ።

ጥቅልል ያለን ጠጉር ዘርዘር ያለ ሚዶ ያስነሳዋል ።

ጥቅልል ላለ ጠጉር ፣ ዘርዘር ያለ ሚዶ ።

ጥበብ ያስከብራል ፣ ሀብት ያስጨፍራል ።

ጥኑ ወዳጅ ጥኑ ጠላት ይሆናል ።

ጥኑ ወዳጅ ጥኑ ጠላት ፣ ጥኑ ጠላት ጥኑ ወዳጅ ይሆናል ።

ጥንቱን ሲሉህ ቡዳ ፣ ቆዳ ይዘህ ሜዳ ።

ጥንቱንም ባልዘፈንሽ ፣ ከዘፈንሽም ባላሳፈርሽ ።

ጥንቱንም የተውሶ ፥ ጠፋ ተመልሶ ።

ጥንቱንም የተውሶ ፥ ጠፋ ጨርሶ ።

ጥንቸል እንደ ዝሆን እሞሃለሁ ብላ ተስነጥቃ ሞተች ።

ጥንቸል እንዳቅሟ ታግታለች ።

ጥንቸልም ለሆዷ ፥ ዝሆንም ለሆዱ ፥ አብረው ውሃ ወረዱ ።

ጥዋት ጀር ማታ ጀር ።

ጥዋፍ ያበራል ፥ ከላሽ ይመራል ።

ጥይት አይር ፥ ፈትል ድውር ።

ጥጃ ሳር ይበላል ፥ ቤቱ እዳ ይሞላል ።

ጥጃ ቢሳሳት ከናቱ ፥ ነገር ቢሳሳት ከጧቱ ።

ጥጃ ቢፈነጭ በሜዳ ፥ ውሃ ቢርጥ በጎድጓዳ ።

ጥጃ ጠባ ፥ ከሆድ ገባ ።

ጥጋበኛንና ውሃ ሙላትን ቁመህ አሳልፈው ።

ጥጋብ ቢሻህ ባቄላ ፥ ኑሮ ቢሻህ ችላ ።

ጥጋብ ቢያምርህ ጠላ ፥ መግዛት ቢያምርህ ችላ ።

ጥጋብን ወደኛ በል ፥ ጥጋበኛን ወዲያ በል ።

ጥጋብን የማይችል አህያ ነው ።

ጥጥ ለፈታይ ፥ ሽልማት ላገልጋይ ።

ጥጥና ሹም እያደር ይከዳል ።

ጦም ከማደር ዳቦ ቀርቅር ።

ጦር ለወረወረ ፥ መሬት ለገበረ ።

ጦር መጣ ሲባል ፥ ሶማያ ቀረጣ ።

ጦር ሲመጣ ፣ ዛቢያ ቆረጣ ።

ጦር እንደ ወረወሩት ፣ ጎራዴ እንደሰነዘሩት ።

ጦር ከወጋው ፣ ምላስ የወጋው ።

ጦር ከፈታው ፣ ወሬ የፈታው ።

ጦርና ጭሬ ፣ አራሽና ገበሬ ።

ጠጣ ምን ትወጃለሽ ? ቢሏት ፣ ከዛፍ ላይ ትግል ።

ጠጣ ፣ ባለቤቱን ታስወጣ ።

ጠጣ ተይዛ ትዘፍን ።

ጠጣና ዝንጀሮ ፣ ተኩላና ቀበሮ ።

ጢሪ ፣ በፈጣሪ ።

ጢት ከበላተኛ ፣ ማታ ከአድመኛ ።

ጢት ከበላተኛው ፣ ማታ ከጠመኛው ፣ እንደሸመላ ፣ በሁለት ይበላ ።

ጢት ከጀንበር ፣ ማታ ከጨንገር ።

## - ጨ -

ጨረቃ ሲጠፉ ኮከብ አባወራ ይሆናል ።

ጨረቃ ብትደምቅ ፣ አትሞቅ ።

ጨረቃና ሴት ፣ ዛሬ ብርሃን ነገ ፅልመት ።

ጨቅጫቃ ሚስትና የሚያፈስ ቤት አንድ ናቸው ።

ጨካኝ ሰይጣን መሳይ ።

ጨካኝና ጨስ መውጫ አያጣም ።

ጨዋታ ለአዋቂ ፣ ወሬ ለጠያቂ ።

ጨዋታን አዳምጦ ፥ እህልን አላምጦ ።

ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ ፥ አለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይጥሉሃል ።

ጨው ሻጭ በገበያ ፥ ጦር በሰማያ ።

ጨው ቢያልጥ በምን ይጣፍጣል ? ዳኛ ቢያዳላ በምን ይሟገቷል ?

ጨው የሌለው ምግብና ሰው የሌለው ሰው አንድ ነው ።

ጨውና በርበሬ ፥ ጀሮና ወሬ ።

ጩኸት ለሲላ ፥ መብል ላሞራ ።

ጩኸት ለቁራ ፥ መብል ላሞራ ።

ጫማ ምንም ወርቅ ቢሆን ከእግር በታች ነው ።

ጫን ካለ ጫን ይፈጃል ።

ጫን ያለው ኮርቻውን ፥ ለምን ያለው ስልቻውን አያጣውም ።

ጫንቃዩን ተገርፈ ፥ ጨርቁን ተገፍፈ ።

ጭልፊትና ሲላ ተጋብተው ጉጉት ወለዱ ።

ጭምት ያበደ እንደሆን የጤፍ ቆረን ደኑ ።

ጭንቅ አልጋ ያስተቃቅፋል ።

ጭድና ጭቃ ፥ ቡሃና ቦቃ ።

ጮኸ የማታውቅ ወፍ አንድ ቀን ብትጮህ እለቁ እለቁ አለች ።

ጮሌ ሲያረጅ መጋዣ ይሆናል ።

## - ጳ -

ጳጉሜ ሲወልስ ፥ ኀተራህን አብስ ።

ጳጉሜን ሲወልስ ፥ ገበሬ ኀተራህን አብስ ።

ጳጉሜ ቢለግስ ኀታህን አብስ ።

ፀሃይ ሳለ ሩጥ ፡ አባት ሳለ አጊጥ ።

ፀሃይ ብልጭ ፡ ወፍ ጭጭ ሲል ።

ፀሃይ ካልወጣ ፡ ከሰፈረበት አይነሳ አንበጣ ፡ ሴት ምክንያት አታጣ ።

ፀሃይ የጧት ፡ አዱኛ የሽበት ።

ፀሃይ ያየውን ሰው ሳያየው አይቀርም ።

ፀሃይና ንጉስ ሳለ ፡ ሁሉም አለ ።

ፀሎት በፆምና ፡ ነገር በደመና ።

ፀሎት በፍቅር ፡ ሃይማኖት በምግባር ።

ፀሎት ከፍቅር ፡ ሃይማኖት ከምግባር ይበጃል ።

ፀሎት ያለ ፍቅር ፡ ሃይማኖት ያለ ግብር አይረባም ።

ፀፀት ፡ እያደር ይመሰረት ።

ፃድቃን ካልተቃጠሩበት ስፍራ ይገናኛሉ ፤ ሀጥአን ግን ከተቃጠሩበት ይተጣጣሉ ።

ፅዋ በተርታ ፡ ስጋ በገበታ ።

ፅድቁ ቀርቶ በውል በኮነነኝ ።

ፅድቅ ለመንኳሽ ፡ ቀኝ ለከሳሽ ።

ፆም ገዳፊና ሰው ጠባቂ ለጥቂት ይሳሳታል ።

ፆማ ፆማ ለፀሎት ሀሙስ ፡ እርጎ ትልስ ።

ፈላ ገነፈለ ፣ ተሞላ ጎደለ ።

ፈረሰኛ ሲሮጥ ፣ እግረኛን ምን አቆመው ?

ፈረሰኛ የወሰደውን ፣ እግረኛ አይመልሰውም ።

ፈረሱም ይኸው ፣ ሜዳውም ይኸው ።

ፈረስ ሲያጠብቅ ፣ ልጓም አይለቀቅ ።

ፈረስ በራሪ ፣ በቅሎ ሰጋሪ ።

ፈረስ ቢያነክስ ፣ አህያ ታጉዝ ።

ፈረስ ቢጠፋው ፣ ኮርቻውን ገልቦ አየ ።

ፈረስ አውቃለሁ ፣ ስገታ እወድቃለሁ ።

ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም ።

ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል ፤ በቅሎ ጥሎ ይረግጣል ።

ፈረንጆች እንደመርፌ ይገቡ ፣ እንደዋርካ ይሰፉ ።

ፈሩ ፈሩ ፣ ማጀት አሩ ።

ፈሪ ለእናቱ ይገባል ።

ፈሪ ለእናቱ ፣ ጀግና ለጀግንነቱ ፣

ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል ።

ፈሪ እንዳይሉኝ አንድ ገደልሁ ፤ ጀግናም እንዳይሉኝ አልደገምሁ ።

ፈሪ ካልጋ ላይ ይወድቃል ።

ፈሪ የሚያባርረው ሳይኖር ይሸሻል ።

ፈሪ የናቱ ልጅ ነው ።

ፈሪ ፈራና እጉድባ ቢኛ ፣ ጀሮውን በላው ያይጥ ቀበኛ ።

ፈሪና ንፋግ እያደር ይቆጨዋል ።

ፈሪን በውሃ ውስጥ ያልበዋል ።

ፈርተው ድንጋይ ቢጥሉ ፣ ጅብ ወጣ ከዱሩ ።

ፈስ ያለበት ቂጥ ዝላይ አይችልም ።

ፈትል ሲረዳዳ ፣ አንበሳ ያስቀራል ።

ፈጅቶ ከሚያጠግበኝ ፣ እስቲበርድ ይራበኝ ።

ፈጣሪን የሚያህል ጌታ ፣ ርስትን ያህል ቦታ ።

ፈጥነው የገመዱት ፣ ፈጥኖ ይበጠሳል ።

ፈጥኖ መስጠት ፣ ሁዋላ ለመፀፀት ።

ፈጭታ የነበረች ፣ ላመልማሎ ኮራች ።

ፉት ቢሉት ጭልጥ ።

ፊተኛው ወዳጅህን በምን ቀበርከው? በሻሽ ፤ ምነው? ሁዋለኛው እንዳይሸሽ ።

ፊት የተናገረን ሰው ይጠላው ፣ ፊት የደረሰን ወፍ ይበላው ።

ፊት የወጣን ጆሮ ፣ ሁዋላ የበቀለ ቀንድ በለጠው ።

ፊት ያሞጠሙጧል ፣ ሁዋላ ይስሟል ።

ፊት ያሞጠሙጧል ፣ ሁዋላ ያፏጯል ።

ፊት ጆሮ ይፈጠራል ፣ ሁዋላ ቀንድ ይበቅላል ።

ፋሲል ሲፈርስ ፣ ጎንደር ይታረስ ።

ፋሲካ የሌለው ጠም ፣ ደስታ የሌለው አለም ።

ፋሲካን ሊያገኙ ፣ ሁዳዴን ይመኙ ።

ፋቂ ቁርበቱን ፣ አናጢ እንጨቱን ።

ፌቆ ስትዝል ፣ አትፈራ ገደል ።

ፌንጣ ብትቆጣ ፣ እንድ እግሯን ታጣ ።

ፌንጣ ብትቆጣ ፣ እግሯን ጥላ ሄደች ።

ፍረድ ለነፍስህ ፣ ብላ ለከርስህ ።

ፍሬ ለመብል ፣ ስንቅ ባገልግል ።

ፍርዱ ገምዳይ ፣ እውነት አጉዳይ ።

ፍርድ ለልጅ ፣ ጥራቢ ለደጅ ።

ፍርድ ለተቀማጭ ፣ ወጥ ለቀላዋጭ ።

ፍርድ አያውቅ ዳኛ ፣ ተገን አያውቅ እረኛ ።

ፍርድ እንደ አሉላ ፣ ፅድቅ እንደ ላሊበላ ።

ፍርድ ጎደለ ፣ ድሃ ተበደለ የሚል ንጉስ አይታጣ ።

ፍርድና ፍትፍት ፣ በየፊት ።

ፍርድና ፍትፍት ፣ ወደፊት ።

ፍቅር ሲጠና ቆሎ ያንርሳል ።

ፍቅር ያስራል ፣ እውቀት ያስከብራል ፣ ጥበብ ያኮራል ።

ፍቅርህን የፈለገ ፣ ልጅህን ፤ ጥልህን የፈለገ ፣ የላም ልጅህን ።

ፍትፍት ለልጅ ፣ ጥራጊ ለደጅ ።

ፍንከች ፣ ያባ ቢላዋ ልጅ ።

ፍንጥር ፍንጥር እንደ ሽምብራ ፣ ያባ ምንይዋብ ፉከራ ።

ፍየል ሁለት ወልዳ አንዱ ለመፅሃፍ ፣ አንዱ ለወናፍ ።

ፍየል ሳምስት ፣ ዶሮ ለባልና ሚስት ።

ፍየል መንታ ትወልድና አንዱ ለወናፍ ፣ አንዱ ለመፅሃፍ ።

ፍየል በልታ ፣ በበግ አበሰች ።

ፍየል ከመድረኳ ፣ ቅጠል መበጠሷ ።

ፍየል ወዲህ ፣ ቅምዝምዝ ወዲያ ።

ፍየል የለኝ ፣ ከነብር ምን አጣላኝ ።

ፍየልና ቀበሮ ፣ ምጥማጥና ዶሮ ።

ፍየሏን እንደ በግ ።

ፍዳ ለሀጥአን ፣ እሴት ለፃድቃን ።

ፍጥም አያናግር ፣ የጎርፍ ሙላት አያሻግር ።

ፍጥም አፍራሽ ፣ ቤተክርስቲያን ተኳሽ ።

ፍጥም ያቆማል ፣ እርቅ ይጠቀልላል ።

ፍጥም ያውላል ፣ አቧራ ያስላል ።

ፎክሮ መሸሽ ፣ ታሪክ ያበላሽ ።

# የቃላት መፍቻ

(ቃሉ የሚገኝበት ገፅ እጎኑ ይገኛል)

ሁዳድ 24,196 — ሰፊ እርሻ

ላዋይ 27 — በእንስት ፆታ የምትጠራ የቤት ውስጥ ቆሌ

ላዳን 76 — ከቁና የሚበልጥ የእህል መስፈሪያ

ልቅ 82 — ልቃቂት

ልበ ሳንባ 36 — በደረቱ አካባቢ ቀይ የሆነ

ልባልባ 36,52 — ጌጠኛ የሴቶች ቡሪ

ለኮ 30 — የፈረስ ፣ የበቅሎ መሳቢያ ጠፍር

መልከኛ 39,102,121,144
145,221 — በዱሮ ጊዜ ንጉስ ርስት እየሰጠ የተከለውና ከቀን ብዛት እንደ ባላባት የተቆጠረ

መቀናጆ 39,175 — በወንፊል የመጣ በሬ

መቃን 41, — በቤት በር ግራና ቀኝ ያለ አራት ማእዘን እን ጨት

መቋደሻ 96 — ቁርስ

መበለት 41,96,140,158,178
218,231 — መነኩሲት ፣ እማሆይ ፣ አሮጊት

መናጆ 42 — ተከታይ

መናፍቅ 141,211 — ተጠራጣሪ (ለሃይማኖት)

መን 69 — ሸማ መስሪያ እቃ

መንጓላ 145 — ንፍጣም

መዘለፊያ 176 — ጥልቆ ፣ አነስተኛ መጥረቢያ

መዳሮ 127 — ድር ማድሪያ

መጋዞ 121 — የምርቱን ውጤት ከባለ መሬቱ ጋር ለመካፈል አራሹ የሚያደርገው ስምምነት

መጋገር 251 — የጭነት ፈረስ

መግላሊት 171 — የማሰሮ መክደኛ

መጭ 40 — ኑግ የሚመስል አረም ።

ሙሬ 56 — የወፍጮ መጥረጊያ

ሙር 200 — በእውቀት ብዛት እንደ እብድ የተቆጠረ

ሙተራ 219 — በጎጃም ውስጥ ያለ ተራራ

ሙሴ 224 — የማህበር አለቃ

ማህሌት 68 — በክብሮና በፅናፅል እየታጀበ የሚቀርብ መንፈሳዊ መዝሙር

ማህደረ ማርያም 124 — በጎንደር ያለ ደብር

ማርያም ውሃ 124 — በጎንደር ያለ ቀበሌ

ማቅ 45,108,212 — ከበግ ፀጉር እንደ ብርድ ልብስ ሆኖ የሚሰራ

ማቶት 152,245 — ከሳር ከልጥ የሚሰራ የእንስራ ወይም የጋን ማስቀመጫ

ማዘንት 91 — በምድጃ ዙሪያ በጭቃና በድንጋይ የሚሰራ የወጥ እቃ ማስቀመጫ

ሜሮን 189 — ቅብአ ቅዱስ

ምርቅ 47,92,121,128 — እንደ ገብስና ስንዴ ባሉ እህሎች ላይ ያለ ሻካራ ቀጫጭን እሾህ

ምስለኔ 34,47 — በፊውዳሉ ስርአት የነበረ ሹም

ምንደኛ 189 — በሰው ቤት ተቀጥሮ የሚሰራ እረኛ

ምዝግዝግ 231 — የተወረወረ ፣ የተምዘገዘገ ዱላ ፣ ዘንግ

ሞረት 44 — በመርሃ ቤቴ የሚገኝ የሃገር ስም

ረጃት 108,219 — ከዘር ለልጅ ያለፈ ገንዘብ ወይም ቅርስ

ረጋ 34 — ከትውልድ ያገኘው ሳይሆን ከሸክላ ሰሪዎች በመማር ሸክላን ወይም ብረትን የሚሰራ

ርቦ 66,78 — አንድ አራተኛ

ሮቃ 53 — የብርብራ አይነት ዛፍ ፍሬው ሲበሉት የሚሆመጥጥ

ሰርተት 118 — ጎተት

ሰሳ 138,164 — ፍየል የሚመስል የዱር አውሬ

ሰናፊል 226 — የድሮ ዘመን ሱሪ ፣ ቡላሌ ፣ ተንፋንፍ

ሰግዳዳ 95,148 — ሰዋራ ድብቅ ስፍራ

ሱፋጭ 46 — ስለታም ድንጋይ

ሲላ 200,251 — ያሞራ ስም

ሲቀጣጠብዋት 232 — ሲያላግጡባት ፣ ሲያታልሏት

ሳታት 62 — የሌሊት ፀሎት

ስሉስ 36 — ሶስት ምስክር

ስማርድ 83 — የነብር ወጥመድ

ስንቆ 41 — በክረምት የሚበቅል የጎመን አይነት ቅጠል

ስብቆ 135 — የእጃ አጥሚት

ሶማያ 249,251 — የጦር እጀታ

ሾላ ሜዳ 109 — ባይፋት ክፍል ያለ ቀበሌ

ሾተል 37,38,71,200 — በሁለት ወገን ስለት ያለው ቀጪን ሰይፍ

ቀርቀሬ 71 — ቆላማ የሆነ ቦታ

ቀርበቦ 127 — ከበሬ ግንባር ቆዳ በጋን ቂጥ የተበጀ ሚዛን ፣ ቁና

ቀብቅቦ 145 — የእርሻ መሬትን አለስልሶ

ቀነቀነ 30 — ዘፈነ

ቀንጠፋ 108 — ልብስ የሚቀድ በጫካ ውስጥ የሚገኝ እሾህ

ቀየዷት 134 — የበቅሎን ፊት እግርና ሁዋላ እግር ወይም ፊት እግርና አንገት ማሰር

ቀጠነኝ 86 — ፍርድ ተዛባብኝ

ቀጠና 127,219 — ረሃብ ችግር

ቁልቢጥ 73 — ትንሽ ቁና

ቁረንጮ 137,140 — የቆዳ ብጫቂ

ቁርፍርፌ 148 — ስንጥቅጥቅ

ቁግ 145 — ከጅማትና ከቃጫ የሚሰራ የጅራፍ ጫፍ

ቃጢ 207 — በጣም ትንሽ የሆነች ቁና

ቅሃ 204 — በጎንደር ያለ ወንዝ ስም

ቅንብቢት 44 — በቡልጋ አጠገብ ያለ ቀበሌ

ቅንብቻ 192 — የተረሳና ትርፍ እቃ ማስቀመጫ ፣ ከቆዳ የተሰፋ መናኛ ኮርጀ ፣ አፊ ክፍት ስፌት

ቆረን 251 — አዝመራ የታጨደበት ማሳ

ቆርቶ 66 — በጥቶ ፤ ፈንክቶ

ቋያ 142,184,221 — የበረሃ ሳር ሳይታጨድ ቆይቶ የደረቀ

በለጡብ 98 — በትንሽ መስፈሪያ (የቅቤ ቅል መከደኛ)

በመረገድ 106 — በማህሌት

ቡላድ 142 — ሲፋጭ እሳት የሚወጣው ብርጭቆ መሳይ ድንጋይ

ቡሌ 161 — ዳላቻ መልክ ያለው የከብት ስም

ቢዛቁን 108,215 — ድቁና ቢቀበል ፥ ቢለፋ ፥ ቢደክም

ቢያረምም 59 — ዝም ቢል

ባጥ 209 — ጣራ

ብር 210,230 — የገብስ ወይም የስንዴ አገዳ

ብርብራ 73 — ፍሬው እሳ የሚያስከር የዛፍ አይነት

ብሳና 44,164,213 — በወይና ደጋ የሚበቅል ነቀዛም እንጨት

ብስና 145,152,231 — መጥፎ ጠረን ያለው ግሳት

ብየኛ 148 — በካሳ የሌላውን ገንዘብ የበላ

ቦራ 186 — ቢጫነት ያለው በሬ

ቦና 41 — ድርቅ

ቦቃ 251 — ግንባረ ነጭ በሬ

ቦዝ 34,38 — ዝንጉ የተናቀ

ቧጋች 95,194 — ውድማ ለውድማ እየዞረ የሚለምን

ተሟረ 194 — ሲያውቅ አበድ

ተታታ 195 — ተንነንነ

ተጠማኝ 98 — የሰው መሬት አራሽ

ታርጣጣ 37 — ሰነፍ ውዝፍ ሴት ከተቀመጠችበት የማትነሳ

ትፋዘኹ 133 — ትፋጠጪ

ቶፋ 100 — ወኪል ፥ ገባሪ

ነቁ 165 — የውሃ ጉድጓድ

ነዳይ 27 — ድሃ (ምስኪን)

ነጠር 90 — ነፍስ ወከፍ

ንዳማ 105 — ቁጭት

አለብላቢት 62 — ሲነኩት የሚያቃጥል ቅጠል

አላል 144 — የጭነት ማስተካከያ ፣ ተጨማሪ ጭነት፣መጣያ

አሜኬላ 31 — የእሾህ አይነት

አምበራስ 143 — ያምባ ሹም ዋና ግንባር ቀደም

አምዛ 151 — ወፍራም የጤፍ እንጀራ

አራድማ 48 — በመንዝ ውስጥ ያለ አገር

አሰድ 112 — የኮከብ ስም በእሳት የሚመሰል

አሳጅ 200 — የጎን ስጋ

አሸን 203 — ክረምት አግቢ

አሸክት 32 — ሻካራ ፣ ቁርንድድ

አቃቢት 54,113 — ግብር የምትፈጭ መነኩሲት

አቃቤ 159 — ዘበኛ ፣ ጠባቂ

አቢላማ 26,85 — ላም ጠባቂ እረኛ

አባሎ 198 — ለጠላና ለወተት እቃ ማጠኛ የሚሆን የዛፍ አይነት

አባ ምንይዋብ 255 — በአጤ ምኒሊክ ጊዜ የነበሩ ጨዋታ አዋቂ ሰው

አብርጣም 80 — ሹርባ

አብሾ 184 — ወፈፍ የሚያደርግ አብሽ መሳይ ፍሬ

አብቹ 44 — በምእራብ ሸዋ ያለ ቀበሌ

አትቀ ታተር 95 — አትሮካከር

አንቃ 116 — ሙጫው እንደ እጣን የሚሸት የዛፍ አይነት

አንጋዳ 139,198 — ጠመዝማዛ

አንጣሪያ 119 — መሬት ለመሬት እያደገ የሚዘምት ቅጠል

አዘዞ 120 — በጎንደር ውስጥ ያለ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም

አጉራ 90 — የበረት መዝጊያ

አግሬ 120 — ትልቅ ጋሻ

አጎዶ 127 — የከሰል ጉድጓድ
አጣሪ 97,107,124 — ቸርቻሪ ነጋዴ
አፅቅ 165 — የአበባ አንጓ
አፈላማ 147 — ከብት አዝመራ ሲበላ የሚከፈል እዳ
አፍላል 151 — ከሸክላ የሚሰራ ማሰሮ መሳይ ድስት
አፎት 37,71,102,138 — የሰይፍ የጎራዴ መከተቻ ፣ ቤት ፣ ሰገባ
እመ 113 — እማሆይ
እርከፍከፎ 75 — ካፊያ
እርኮት 141 — ከቆዳ የተሰራ የውሃ መያዣ
እርያ 129,201 — በዱር የሚኖር ያሳማ አይነት አውሬ
እቡይ 200 — ትእቢተኛ
እናርያ 245 — የቀድሞው የኢትዮጵያ ደቡብ ምእራብ ግዛት መጠሪያ ስም ፣ በወላይታ ፣ በሲዳሞ ፣ በኩሎ ፣ በኮንታ የሚኖር ነገድ
እንበለ (ማእዝ) 133 — ያለ
እንባሮ 124,170,210 — የእንጨት አይነት
እከት 108 — ቅራቅንቦ እቃ
እይር 249 — ቅልቅል
ከርከሬቫ 223 — ፍጅት ፤ ጠብ
ከፈር 179 — እንቅብ
ኩርዲዳ 220 — ብርቱ አራዊት ገሪ
ኩተት 150 — ቁንጮ
ካምሱር 89 — በጦር መሳሪያ ውስጥ ክብሪታዊ ባህርይ ያለ ውና ቃታው ሲወጋው ጥይቱን የሚያቀጣ ጥል አካል ።
ካይላ 190 — በጎንደር የሚገኝ ነገድ
ኮሸሽላ 75 — በወይና ደጋ የሚበቅል እሾሀማ እንጨት
ኳደሬ 65,158 — ገባርን እያዘዘ ስራ የሚያሰራ ሹም
ወለባ 29,36,52,158 — በወይዛዝርና በመኳንንት ፀጉር ላይ የሚሰካ የራስ ጌጥ

ወለፊንድ 202 — ጠማማ
ወሶ 34 — ጎሽ 1 እሰይ
ወቂራ 37 — ጩቤ
ወባራ 136,172,192 — ቀበጠ
ወታቦ 127,232 — ከእበትና ካመድ የተሰራ ጎድጓዳ እቃ
ወንጋራ 208 — ወልጋዳ
ወንጠፍት 243 — የጠላ የቅቤና የዘይት ማጥለያ ወንፊት
ወንጭት 97 — በደራና በመርሃቤቴ መሃከል ያለ ጅረት
ወዘት 41,74 — እሳት አጠገብ መቀመጥ
ወይኖ 161 — የወይንማ በሬ ስም
ወደረ 124 — ጥርቅም አርጎ ያዘ
ወጀድ 70 — የአትክልት ስፍራ፥ባጥር በቅጥር የተከበበ ቦታ
ወጋሪ 112 — አሳን ወርውሮ በድንጋይ ላይ የሚከሰክስ
ወጭት 97,163,212 — ጣባ
ዋልድባ 118 — በጎንደር ውስጥ ያለ ታላቅ ገዳም
ዋቢ 164 — ሰጪ ፥ አቀባይ
ዋንዛ 164 — ፍሬው የሚበላ እንጨቱ የማይነቅዝ ዛፍ
ዋግ 67,158 — የሰብል በሽታ
ውኸርምኸርም 186 — ረኸርም ፥ ጎታታ
ውኸርሞ 80 — ውስጠ ክፍት እንጨት ወይም መቃ ለጋያ መጠጫ የሚሆን
ዘለሳ 173 — ቁጥቋጠ ምልመላ
ዘማ 200,205 — አመንዝራ
ዘባን 171 — ጀርባ
ዘባጣ 37,231 — ረባዳ ቦታ
ዛብ 170,173 — ለፈረስ ለበቅሎ እንደ ልጓም ሆኖ የሚገታ
ዝማሜ 30 — በመቋሚያ እየተወዛወዙ የሚዘመር መንፈሳዊ መዝሙር
ዝባድ 170 — ጥሪኝ ከምትባል አውሬ የሚገኝ የሽቱ ቅባት

ዘላ 203 — ሰነፍ

ይብራ 225 — ውሃ ውስጥ ጠልቃ የምትወጣ እግረ ቀይ መልከ ብዙ የውሃ ዶሮ

ይቶት 31 — መነኩሲት ፤ እማሆይ

ይኮርታል 101 — ይጎራል

ይዋጂ 61,89,154 — ይገዛ

ይጋጃል 192 — ይበላሻል

ደለማ 63 — ጨለማ ፤ ሰዋራ

ደልሰ 91 — በለፀገ

ደረባ 215 — የጎተራ ጣራ

ደረጣ 34 — ሁከት

ደራል 144 — የእንጨት አይነት

ደባይ 142 — ሰፊ ነጋሪት

ደንካራ 145 — ደካማ ፤ አላዋቂ

ዳሞትራ 144 — የሚናደፍ ጥቁር መርዘኛ ሸረሪት

ዳንዴ 201 — ቀማኛ

ዳወሮ 137 — የቀድሞ ሃረርጌ ስም

ዳፋ 172 — ጠንቅ

ድርጎ 231 — ጉርሻ

ድርጭት 149,231 — ከርግብ የሚያንስ ወፍ

ድበላ 231 — ባቄላ ፤ አተር ፤ ምስር ፤ ከገብስና ስንዴ ቅል ቅል የሚጋገር እንጀራ

ድጉስ 66,226 — ማህደር ፤ አፎት

ዶሰኛ 191 — ሃይለኛ

ዶባ 68 — የበረሃ ቀንደ ረዥም በሬ

ዶጮ 74 — ከገንቦ የሚያንስ የሸክላ እቃ ፣ የጠጅ የጠላ ፣ የውሃ ማኖሪያ

ጀላፋ 188 — ሰነፍ

ጀንፎ 168 — በዘንግ ጫፍ ላይ የሚሰካ ጥምጥም ብረት

ጀጀባ 199 — በወንዝ ዳር የሚበቅል ፍሬው የሚበላ ዛፍ

ጃኖ 159 — በስፌ ቀይ ጥለት የተሰራ ዝቅዝቅ ልብስ

ገለፈንት 235 — በሆነው ባልሆነው የምትስቅ

ጉልላት 37,91 — በዘውድና በአክሊል ምሳሌ የተሰራ ሸክላ ፣ በድንኳን በቤተክርስቲያን ጫፍ የሚሰካ

ጉልማ 121 — ላሽከር፣ለሎሌ፣ለዘመድ፣ለወዳጅ ተከፍሎ የተሰጠ ማሳ

ጉጣ 62 — የማረሻ እላቂ

ጊጉይ 180 — አመፀኛ ወንጀለኛ

ጋት 68 — ውስጥ እጅ ፣ መዳፍ

ጋይ 240 — አፈሩን በማቃጠል የሚደረግ ባህላዊ የእርሻ ማዳበሪያ

ጋፍ 194 — ሞኝ

ጌኛ 44,166 — መጋዣ ፈረስ

ግልምቢጥ 168 — የተገላቢጦሽ

ግጫ 156 — የሳር አይነት

ጎታ 215,228,247 — ከመቃ ወይም ከቀርከሀ እንደ ቅርጫት የተጎነጎነ የእህል ማስቀመጫ

ጎዳ 73,144,186,244 — የተጎዳ ፣ ቀላሳ ከብት ፣ ዱልዱም

ጎንጅ 36 — በጎጃም የሚገኝ የታወቀ የቅኔ ትምህርት ቤት

ጎፍላ 35 — መርገፍ ፤ ጌጥ

ጠራቂ 102,155 — በያጅ ፤ ብረት አልባሽ

ጠገራ 72 — በራሳም እንጨት ቀዳዳ የተዋደደ መፍለጫ

ጥቅንጥቅ 101 — ውስብስብ

ጥንቅል 22 — ቁንጣሪ

ጩንቋራ ,199,222 — ሸውራራ

ጩንገር 250 — የዛር ስም

ጭራንፎ 222 — የጭራሮ ጫፍ

ጭሬ 250 — ቅጠለ ጠባብ ጦር

ጭቃ 34,85, — ቀደም ሲል የነበረ የሹመት አይነት የቀበሌ ሹም

ፈርዛዛ 127,159,199 — ደስተኛ

ፈግጡት 90 — ተዉት

ፈጠም 187,195,256 — የነገር መግቻ

ፈፋ 31 — የውሃ መውረጃ

ፉቅራ 180 — የእስላም ቃልቻ

ፌራ 206 — ወረርሽኝ ፣ ተላላፊ የተስቦ በሽታ

ፌቆ 135,254 — የሰስና የሚዳቋ አይነት የዱር ፍየል

ፍንጅ 126,129,247 — እንደ ካቴና ያለ የእጅ ማሰሪያ

ፎገራ 26 — በጎንደር ያለ ቀበሌ